# በተማሪዎች መብት ጥበቃ ሥር ተሻሽሎ የወጣ የመብት ማስታወቂያ
## (Notification of Rights Under the Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA))

ይህ ማስታወቂያ፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎችን (ከእድሜ ገደብ ግዴታ የተላቀቁ እና አናሣዎች ወይንም 18 ዓመት የሞላቸው ወይንም ከዚህ በላይ የሆኑ) አሰሳ መጠይቆችን የማካሄድ መብቶቻቸውን፣ መረጃዎችን ለገበያ አገልግሎት ተግባር መሰብሰብ እና ሥራ ላይ የማዋል፣ አንዳንድ የሰውነት ምርመራዎች ማካሄድን ይመለከታሉ። እነዚህ መብቶች ለተማሪዎች መብቶች ጥበቃ (*Protection of Pupil Rights Amendment* (20 U.S.C. § 1232h; 34 CFR Part 98) በግልጽ ተብራርቶላቸዋል። ሕጉ እና ደንቦቹ እንደ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የመሳሰሉ (DCPS) የትምህርት ተቋማት፣ ለወላጆች እና ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ስለ መብቶቻቸው እንዲያስታውቁ ይህም፤

1. *ተማሪዎች የሚከተሉትን አንዱን ወይንም ከዚህ በላይ የሆኑትን በሕግ የተጠበቁ መስኮችን ("በሕግ የተጠበቁ የመረጃ አሰሳ መጠይቅ")* ("protected information survey") አሰሳ መጠይቁ በሙሉ ወይንም በከፊል በዩኤስ የትምህርት መምሪያ (U.S. Department of Education (USDE) የሆኑትን ተማሪዎች አሰሳ መጠይቁን ለማቅረብ ከመስማማታቸው በፊት

   - የተማሪው ወይንም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ወገንተኛነት ወይንም እምነት፤
   - የተማሪው ወይንም የተማሪው ወላጅ የአእምሮ ወይንም የሥነ ልቦና ችግሮች፤
   - ስለ ጾታዊ ባህርይ አመለካከት፣ ዕውቀት፣ ግንዛቤ ወይንም ያለ ግምት፤
   - ሕገ ወጥነት፣ ፀረ ማኅበራዊነት፣ ራስን መወንጀል፣ ራስን የማቃለል ባህርይ፤
   - ምላሽ ሰጪዎች፣ የቅርብ የቤተሰብ ዝምድና ስላላቸው ሌሎች ሰዎች ከፍተኛ ሂስ፣ ግምገማ
   - እንደ ከጠበቆች፣ ከዶክተሮች ወይንም ከሚኒስቴሮች ከመሳሰሉ ጋር ያለ ሕግ ያወቀው እና የተቀበለው ልዩ የተዛምዶ መብት፤
   - የተማሪው ወይንም የወላጆች ሃይማኖታዊ ልምዶች፣ ሃይማኖታዊ እምነቶች እና፤
   - ለፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን በሕግ ከሚጠይቀው መለኪያ ሌላ ገቢ ፤

2. *ተማሪ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የማስቀረት አማራጭ እና እድል ሊኖረው የሚያስችል ማሳሰቢያ ማግኘት፦—*

   - የገንዘብ ምንጮ ከየትም ይሁን ማናቸውም ሌላ ተጠብቆ የተያዘ የመረጃ አሰሳ፤
   - የተማሪውን አስቸኳይ የጤንነት እና ወይንም የደህንነት ሁኔታን ለመጠበቅ አስፈላጊ ሳይሆን፣ ከመስማት፣ ከማየት ወይንም የጀርባ አከርካሪ አጥንት በስቴት ሕግ ሥር በተፈቀደው ወይም በሚፈለገው መሠረት ማናቸውም አስቸኳይ ያልሆነ ውስጣዊ የማንነት ገበናን የማያጋልጥ (scoliosis) ትምህርት ቤቱ ወይም ወኪሉ የሚያካሂደው የአካል ደህንነት ማጣሪያ ምርመራ እና፤
   - ማናቸውም ዐይነት ከንዋኔ፣ ግላዊ የሆኑ መረጃዎችን ለገበያ ወይንም ለሽያጭ አገልግሎቶች ለማቅረብ የሚያካትት፤ አለበለዚያም ሌሎች መረጃዎችን ለማሰራጨት (ይህ ለአንድ ለተወሰነ የግል ዐላማ አገልግሎት ብቻ ከተማሪዎች፣ መረጃዎችን ለማሰባሰብ፣ ይፋ ለማድረግ፣ ለማዳበር፣ ለመገምገም ወይንም ለትምህርት መሣሪያዎች ወይንም ለትምህርት አሰጣጥ አገልግሎቶች ተግባር አይውልም።)

3. *ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜና የሚከተሉትን ሥራ ላይ ከማዋል እና ወይንም በእነዚህ ከመጠቀም በፊት ወላጅ ስለ መቆጣጠር መብቱ ማሳሰቢያ ማግኘት—*

   - ተጠብቆ የተያዘ የተማሪዎች አሰሳ መጠይቅ እና በሦስተኛ አካል የተፈጠሩ አሰሳ መጠይቆች፤
   - ከላይ ስለተጠቀሱት የገበያ፣ የሽያጭ፣ ወይንም በሌሎች የስርጭት አገልግሎቶች ምክንያት ከተማሪዎች ግላዊ መረጃዎችን ለማሳሰቢያ ሥራ ላይ የዋሉ መሣሪያዎች፣ እና
   - እንደ ሥርዓተ ትምህርቱ አካል አገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መሣሪያዎች።

ዲሲፒኤስ፣ የሕግ ጥበቃ መብት ያላቸውን አሰሳ መጠይቆች በማሰባሰብ፣ ይፋ በማድረግ፣ ወይም የግል መረጃዎችን ለገበያ፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ የስር ጭት አገልግሎቶች የማዋልን መብቶች በሚመለከት ፖሊሲዎችን ነድፋል፣ እንዲሁም የተማሪዎችን የግል መብት ለመጠበቅ ሁኔታዎችን አመቻ ችቷል። ዲሲፒኤስ በተጨማሪ፣ የአሰሳ መጠይቅ መካሄጃ ጊዜያቱ በየዓመቱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ወላጆች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች እንዲያውቁ ያደርጋል። ስለተወሰኑ ወይ ንም ስለ አማካይ ቀናት የሚከተሉት ክንውኖች ስለሚካሄድባቸው ጊዜያት (ተማሪዎች ከክንዋኔዎቹ ተሳትፎ የመውጣት አማራጭ እንዲኖራቸው በማድረግ ጭምር)—

- ለገበያ፣ ለሽያጭ ወይንም ለሌሎች ስርጭቶች ተግባር የግል መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ለሌሎች ይፋ ማድረግ እና ሥራ ላይ ማዋል
- በ USDE በሙሉም ይሁን በከፊል በገንዘብ ያልተደጎመ እና ያልተደገፈ፣ በሕግ የተጠበቀ መረጃ ሥራ ላይ የማዋል እና
- ከላይ ተብራርቶ በቀረበው መሠረት አስቸኳይ ያልሆነ ማናቸውም የሰውነት ምንነትን የማያጋልጥ የአካል ምርመራ ማጣሪያ

የዲሲፒኤስ ፖሊሲዎች ከ PPRA መብቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው፣ እንዲሁም የአሰሳ መጠይቁ መካሄጃ ቀን ጭምር የሚከተለውን ድረ ገጽ በመቃኘት መጠቀም ይቻ ላል፤ http://dcps.dc.gov/page/conduct-research-or-obtain-confidential-data ከዚህም በተጨማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ከ PPRA መብቶች እና አሰሳ መጠይቁ መካሄጃ ወቅት ጋር ተዛምዶ ስላላቸው ዲሲፒኤስ ፖሊሲዎች የክልል ትምህርት ቤቶቻቸውን ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

መብታችን ተነክቷል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች አቤቱታቸውን ለሚከተለው ማቅረብ ይችላሉ፡—

Family Policy Compliance Office
U.S. Department of Education
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-4605